

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከዲሴምብር 1-31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

## እንዲሁም

## ከጃንዋሪ 1-31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 2026

አዲስ አበባ


ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፈው የዲሴምበር ወር ለበጋ ዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ የተሻለ ገጽታ ነበራቸው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የተስፋፉ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በመሆኑም፤ በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ዝናብ የሚያገኙት የደቡብ ኦሮሚያ፣ የደቡብ ሶማሌ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል። በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል። በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ10 ሚ.ሜ በላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አርባምንጭ 43.8፣ አዋሳ 45፣ ኮምቦልቻ 11.1፣ ደበረ ማርቆስ 12.5፣ 40.7፣ ድሬዳዋ 17.3፣ ጅማ 59.2፣ 24.4፣ 12፣ 11.6፣ ነቀምት 21.3፣ አማን 27.5፣ 19.6፣ 19.6፣ አርሲ ሮበ 10.3፣ አርጆ 10.4፣ 16.4፣ ባቲ 36፣ ብላቴ 50.3፣ ቦሬ 18.5፣ ጨፋ 27፣ ጭፍራ 10.2፣ ጭራ 14፣ ፉኝዶ 21.4፣ ጋምቤላ 21.1፣ ገቲራ 18.3፣ 11.3፣ 22.7፣ 13.2፣ 24.3፣ ገለምሶ 34.8፣ 14.2፣ ጊዳ አያና 18.1፣ ጊኒር 15፣ ጊምቢ 16.2፣ ወሊሶ 12.6፣ ሆሳና 15.2፣ እምድብር 13.3፣ 13.8፣ 23.4፣ ጅንካ 18.8፣ 18.2፣ 48.8፣ 14.8፣ ካቺሴ 20፣ ኮንሶ 27.2፣ 12.7፣ 12.5፣ ማጀቴ 13.2፣ ማጂ 12.8፣ ማሻ 50.4፣ ሞሌ 36.4፣ ሰኮሩ 10.6፣ ሲሪንቃ 10.2፣ ሰዉላ 12.7፣ 25.5፣ ሰኮሩ 10.4፣ ቴፒ 11.7፣ 16.2፣ ተርጫ 17.2፣ 15.3፣ ወላይታ ሶዶ 26.7፣ 26.2፣ ያቤሎ 15.1፣ አሮርሳ 10.5፣ 15.2፣ 20.3፣ 25.3፣ 10.4፣ ቡልቂ 20.7፣ 10.7፣ 17.6፣ 20.7፣ 16.4፣ 17.4፣ 30.4፣ 17.5፣ 19.3፣ 20.8፣ 11.2፣ 25.1፣ 20.4፣ 26.7፣ ቡርቃ 36.8፣ ደበረ ሲና 16.8፣ ደንገጎ 28.1፣ ዲመካ 18.6፣10.4፣12.5፣ ፎጉ ሌቃ 10.5፣ 11.5፣ ጊናግር 10.8፣ ሃርሲሲ 21፣ ሃሮ 22.2፣ ሆርዶዮ 12.9፣ ቅዳሜ ገበያ 18.6፣ 36.5፣ 22.5፣ ኩሚ 11.8፣ መሆኒ 12፣ መልካ ጀባዱ 12.8፣ መርሳ 16፣ ሲቦ 16.3፣ ትንሹ መጢ 14.3፣ መንደር አስራ አንድ 16፣ 11፣ ኦንጋ 15.7፣ ሺንዲ 32.5፣ 12.5፣ ያዮ 26.2፣ 10.8፣ ይርጋለም 12.6፣ ወንዶ ገነት 10.1፣ 15.2 እንዲሁም ኮረም 13.1 ሚ.ሜ የሚደርስ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡ ፡ በአጠቃላይ ባለፉዉ ወር በሰላሳ አራት (34) የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በሌላ በኩል በሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ሰሜን ምስራቅ

እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 1 )፡፡





ምስል፡1 ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2025 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች


ባለፈዉ ወር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቦረና፣ የምስራቅ ቦረና፣ የጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከሱማሌ ዳዋ እና ሊበን፣ ዞኖች ላይ ከ16-150 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-12 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

በሌላ በኩል  የምዕራብና የምስራቅ ጎጃም፣የአዊ፣ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል ጥቂት የምዕራብ ትግራይ ዞን፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ አርሲ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች. ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ የወላይታ እና ጌዲዮ ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ6-60 ሚ.ሜ የሚደርስ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ከ2-9 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፈዉ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ ኦሮሚያ እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ በአብዛኛዉ መደበኛ እና ከመደበኛዉ በላይ፤ የደቡብ ሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች ከመደበኛ በታች የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴብበር 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴብበር 1 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴብበር 1 እስከ 31/2025 ነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

በሌላ በኩል ባለፈው ወር የበጋው ደረቅ፤ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በተለይም በመጀመሪያዎች አሰር ቀናት በሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛው፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተስተዉሏል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነትም ቡሂ 3.4፣ 2.0፣ 2.2፣ 3.6፣ 4.0፣ 4.0፣ 3.8፣ 4.8፣ 4.0፣ 3.6፣ 4.0፣ 4.6፣ 3.0፣ 4.0፣ ሐሮማያ 3.2፣ 2.0፣ 2.6፣ 4.0፣ 4.4፣ 4.0፣ 3.8፣ 4.0፣ 4.2፣ ወገልጤና 2.5፣ 4.2፣ 4.8፣ 4.6፣ 4.0፣ 4.2፣ 4.0፣ 4.5፣ ጅግጅጋ 3.0፣ 2.5፣ 3.5፣ 4.0፣ 4.5፣ 4.4፣ አርሲ ሮቤ 2.5፣ 2.5፣ 3.0፣ 4.5፣ 4.5፣ አምባ ማሪያም 4.2፣ 4.5፣ 4.0፣ 4.2፣ 4.6፣ 4.8፣ 4.5፣ 3.5፣ 3.6፣ 3.0፣ 3.4፣ 4.0፣ 4.2፣ 4.6፣ 4.8፣ ቢሾፍቱ 3.8፣ 3.0፣ 4.6፣ 4.2፣ 4.0፣ 4.8፣ 4.0፣ 4.2፣ 4.8፣ መሃል ሜዳ 4.8፣ 3.2፣ 4.8፣ 4.2፣ አለም ከተማ 3.2፣ 4.5፣ 4.8፣ 4.2፣ 4.2፣ 4.8፣ 4.2፣ 4.8፣ 4.5፣ ደበረ ብርሃን 3.8፣ 3.8፣ 4.2፣ 3.2፣ 4.6፣ 3.8፣ ሮቤ 4.2፣ 3.4፣ 3.8፣ 4.8፣ 4.8፣ ባቲ 3.4፣ 3.6፣ 4.0፣ 4.6፣3.7 ጅማ 3.8፣ ዳንግላ 4.5፣ 4.0፣ 4.0፣ ቁሉምሳ 4.2፣ እምድብር 4.8 ጨለንቆ 3.8፣ 3.4፣ -2.0፣ -1.0፣ -1.0፣ -2.0፣ 2.0፣ 1.8፣ ኮረም 0.5፣ 3.5፣ ጋሸና 4.2፣ 3.1፣ 3.4፣ 4.3፣ 3.1፣ ዳባት 4.8፣ 4.8፣ 4.4፣ 4.0፣ በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል 2)፡፡





ምስል 2፡ ከዲሴምበር 1-31 በ24 ሰዓት ውስጥ ከአምስት (5) ዲግሪ ሴልሺየስ በታች የተመዘገበባቸዉ ስፍራዎች

## 1.2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የዲሴምበር ወር በተለይም በመጀመሪያዉና በሁለተኛዉ አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የነበረዉ የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የደረሱ ሰብሎች እንዲደርቁ፣ በጊዜ እንዲሰበሰቡና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን ምቹ ሁኔታ ነበረዉ፡፡ በሌላ መልኩ በአንዳንድ የሰሜን፣ የመካከለኛዉና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን የተነሳ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ሲመዘገብ በተወሰኑ ጥቂት ቦታዎች ላይ ደግሞ ከዜሮ ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም የተስተዋለው ቅዝቃዜ በተለይም በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎችና በጓሮ አትክልቶች ላይ በጥቂት ቦታዎች ላይ በተወሰነ መጠን አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በዲሴምበር የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት አልፎ አልፎ ከነበረዉ የደመና ሽፋን በደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ደቡብ ምስራቅና በመካከለኛዉ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት ተመዝግቧል፡፡ ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ አንዳንድ


ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለአትክልቶችና በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለተዘሩ የሸንብራና ጓያ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች፣ ለእንስሳት የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ላይ የተገኘው እርጥበት ጠቀሜታ ነበረው። በሌላ በኩል በሰሜን ምስራቅ አንዳንድ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን ይህም ሁኔታ ለደረሱና በመሰብሰብ ሂደት ውስጥ ለነበሩ ሰብሎች አሉታዊ ጎን ነበረው በተለይም በደቡብ ወሎ ዞን ሰከላ ወረዳ እና በደብረ ማርቆስ በረዶ ቀላቅሎ በጣለዉ ዝናበ በደረሱ ሰብሎች ላይ ጉዳት አድርሷል(ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ዲሴምበር ወር በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ በላይኛው ዋቤ ሸበሌ፣ በመካከለኛው አባይ፣ በጥቂት በመካከለኛው እና ታችኛው አዋሽ እንዲሁም በጥቂት አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ መያዣዎች አዎንታዊ ሁኔታ እንደ ነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ ተከዜ፣ አባይ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ እና መረብ ጋሽ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ በጃንዋሪ ወር የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ሰፍኖ የሚታይበትና ከዚሁ ጋር ተያይዞም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት የሚያሳይበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በጥቂት ቦታዎች ላይ አነስተኛ ዝናብ ይዘንባል፡፡

## 1.1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ

በሚቀጥለው የጃንዋሪ ወር በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ እንደሚኖረው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል በመጀመሪያዎቹ ሳምንታት ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሻለ የደመና ሽፋን የሚኖራቸው ሲሆንና፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ ፡፡

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የጃንዋሪ ወር በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ በመከናወን ላይ ለሚገኘው የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮችና

የሚመለከታቸው አካላት ሰብልን ከማሳ የማንሳትና የማከማቸት እንዲሁም የመውቃት ተግባራትን በማከናወን ምርትን ከብክነት መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ከወሩ በመጀመሪያዎቹ ሳምንታት አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በጥቂት የደቡብ ምዕራብ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምስራቅና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጠበቀው መጠነኛ እርጥበት ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ የበልግ እርሻን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበትን የሚያሻሽል እንዲሁም ለበልግ ወቅት የማሳ ዝግጅትን አስቀድሞ ለማከናወን ጠቀሜታ የሚኖረው ሲሆን በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ለሚገኙ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦትን እንደሚያሻሽል ይጠበቃል፡፡

## 1.3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የጃንዋሪ ወር አብዛኛዎቹ የሀገራችን ተፋሰሶች የበጋው ደረቅ የአየር ሁኔታ ተፅዕኖ ስር እንደሚቆዩ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡